# ኣቶ ስየ ኣብርሃ በሲያትል

ጥቅምት 24 ቀን 2005 ዓ.ም

ነሃሴ 27 ቀን 2004 ዓ.ም የመድረክ ኣባላት በሲያትል ከሚኖሩ ኢትዮጵያዉያን ጋር መወያየታቸዉ ይታወሳል፥ በተለይ ኣቶ ስየ ባደረጉት ንግግር ላይ ከተሰብሳቢዎች ተቃዉሞ ገጥሟቸዋል፡- በቀጣይም በርካታ ሰዎች በዚህ ጉዳይ ኣስተያየት ሰጥተዋል፡-እኔም በወቅቱ የጻፍኩት ቢሆንም ባማርኛ መጻፍ ባለመቻሌ ምክንያት ረቂቁ ኣሁን ድረስ ቆየ፡- ጨርሶ ከሚቀር ዘግይቶም ቢሆን ሃሳቤን መግለጹ ተገቢ ስለሚሆንና ለወደፊቱም የኣቶ ስየ እና ኣሁን ድረስ ስሙን መቀየር ያልፈለገዉ የትግራይ ነጻ ኣዉጪ ወያኔ ጉዳይ በቀላሉ የሚታይ ባለመሆኑ የመታገያ ኣቢይ ኣጀንዳ መሆን ኣለበት የሚል እምነት ስላለኝ ነዉ፡- ባጋጣሚ ኣቶ ስየ ለጱህፌ መነሻ ሆኑ እንጂ ህወሃት ከመበስበሱ በፊት የነበሩ ፖሊት ቢሮ ኣባላት በሙሉ በያሉበት ኣድፍጠዉ ካሉበት ብቅ በማለት በዚህ ጽሁፍ ለቀረቡ ጥያቄዎችና ሃሳቦች መልስ ሊስጡ ይገባል፡-

የኣቶ ስየ ጽሁፍ ይበልጥ ያተኮረዉ መለሰ ዜናዊ እንዴት ሞተ፡-ከዚያስ በሁዋላ በሚለዉ ነጥብ ዙሪያ ነዉ፡-በመግቢያዉም የጠቀሱት የኣሜሪካኗ ኣምባሳዶር ሱሳን ራይስ በቀብሩ ስነሰራት ባደረገቺዉ ንግግር ላይ ነው፤ አጠቅሳለሁ
*__ዲያስፖራዉ ያተኮረው መለስን በማድነቅ በተናገረቺው ላይ ነው__........* ኢትዮጵያውያኑን ያስቆጣው ግን መለሰ ምን እያለ ይስድበን እንደነበር በኣገራቺን ምድር ፡-በመስቀል ኣደባባይ፡- በራሳቺን ቴሌቢዚን ለ25 ደቂቃ ያህል ባደረገቺው ንግግር ነው፡- በመሰረቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ሃዘኑ መሪር ነው እየተባለ የሚቀለደው በወያኔ ኣመራርና በሚያዙበት ሬድዮና ቴሌቪዝን ጣቢያዎች እንጂ ህዝቡ የሚያለቅስዉ ኣንድም በወያኔ የ21 ኣመት ኣገዛዝ ለደረስበት በደልና ግፍ ሌላም በዚህ ዘመን በችጋር ተውጦ ከቀየዉና ከርስት ንብረቱ ከመንደሩ በመፈናቀል ለሚቆጥረው መከራና ኣበሳ ነው፡-

ኣቶ ስየ ግን ባቀረቡት ጽሁፍ እንዲህ ይሉናል ፡-አጠቅሳለሁ *__የመለስ ሞት ይፋ ከሆነ በሁውላ የኣዲስ ኣበባ ህዝብ በድንጋጤና በሃዘን የከረምቱ ዶፍ እየወረደበት ኣስከሬኑን ቤተመንግስት ኣድርሶታል ታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብም አርሙን ኣውጥቶአል__ ......* በማለት የሚገልፁት መለስና ወያኔ የሚስሩትን ድራማ አያስቀጠሉት ነው ለማለት ይቻላል እንደተከታታይ ፊልም ማለት ነው፡-

መለስ ከሞተ በሁዋላ የወያኔ መሪዎች ለራሳቸው ግራ ተጋብተው የሚይዙት ይሚጨብጡት ቅጣምባሩ ጠፍቶባቸው እንዴት ነው ምክንያቱን ኣጣርተው ለኢትዮጲያ ህዝብ ማሳወቅ የሚችሉት፡-ስለገጠማቸው ችግርኮ ራስዎ መልስዉታል ..*__የመለስ ተከታዮች ከዚህ በሁዋላ የሚለዎጥ የለም በነበርበት ይቀጥላል__.....*ማለታቸውን፡-

ወደፊትም የመለስ ተከታዮች ምን ማድረግ እንዳለባቸውም አሳስበዋል ....*__የተጀመረዉን የልማት በጎ ጅማሮ ኣጎልብተዉ ዳር እንዲያደርሱ__...* በማለት ለመሆኑ የትኛዉን ልማት ነዉ የሚያወሩት ኣቶ ስየ--- በሙስና የበከተዉን የወያኔ ኣስተዳደር፡- ኣንድ ክረምት መቁዋቃም የማይችሉት የቻይና መንገዶች ወይስ ደረጃቸዉን ያልጠበቁት ፎቆችና ኮንደምንየም ቤቶች፡- ነው ወይስ መሬትና ኣገርን አየቆረሱ ለባእዳን መሸጡን፡- ለነገሩማ ከአስር ኣመት በፊት መለስ ድርጅቱ መበስበሱን ኣረጋግጦልናል በስበስኩ ማለት አልደፈረም እንጂ ፡- ኣቶ ስየ ሊገነዘቡ የሚገባው መለስን ስልጣን ላይ ካወጡት ኣንዱ ማን ሆነና ነው ሃያ አንድ ኣመት ሙሉ አንደ አብድ ዉሻ /ወገኖቹን ኣልልም በኢትዮጵያዊነቱ ሰለማያምን ወይም ስለካደ/ የኢትዮጵያን ህዝብ ህጻን ኣዋቂ ሳይል ሲጨፈጭፍ ኖረ የዚህን ግማሽ ነበሩበት፡- የስራ ባልደረቦቹንና የትግል ኣጋሮቹን /ሆን ብሎ በስልጣን እንዲባልጉ ካደረገ በሁዋላ/ በማጥፋት በማሰርና በማባረር አርስዎንም ጨምሮ ኣስወገደ አርሶንማ አንደ ጥጃ አያስረ አየፈታ ቀለደብዎት መለስ ሞት ቀደመው እንጂ ኣሁን ያስቀመጣቸውንም ቢሆን ሃይለማሪያምን ጨምሮ ከአራትና አምስት ኣመት በላይ ኣያስቀምጣቸውም ነበር፡- ይህን ባህሪውን ከኣቶ ስየ የተሻለ ውስጥ ኣዋቂ ሊኖር ኣይችልም ታዲያ የዚህን ኣብይ ታሪክ ጉዳይ ሊያሳውቁን ሲገባ በስሞንኛ ሞትና ለቅሶ ዙሪያ ትኩረት ስጥተው ንግግር ብለው ግዜ ማጥፋትዎ በስደት ያለውንና ብሶት የጎዳውን ኢትዮጵያዊ ብቻ ሳይሆን አገር ውስጥ ያለውን ሁሉ በአጅጉ አሳዝኖአል ኣሁንም ለማዘናጋት መሞከርና ድብቅ ኣላማ አንዳለ ኣመላካች ነው፡-

መለስ ከሞተም በሁዋላ ከኢትዮጵያ ህዝብ ላይ በቀላሉ አንደማይላቀቅ ከኣሁኑ አየታየ ነው ፡-በጭካኔ ተግባር ኣስልጥኖ ያስቀመጣቸው ካድሬዎቹና ቡችላዎቹ ሞቱን ማመን ኣቅቶኣቸው ድንኩዋን በየቀበሌው በማስተከል አንደተለመደው የአንቁጣጣሽ ዶሮ መግዣ በመስጠት ኑ ሃዘን ድረሱ በማለት ህዝቡን ሲያንገላቱ አንደስነበቱ የተመለከትነው ኣስቀያሚ ድራማ ነበር፡-የመለስ ስርኣት ገና ከጅምሩ ኣንስቶ ኣስልቺ ድራማ በመስራት ህዝቡ ኣይኑና ጆሮውን አስኪጠላ ድረስ በግድ ተቀበል አየተባለ ሲስቃይ መኖሩን በሚገባ ያውቃ ሉ አንዱንም ድራማ ራስዎ ስለተጫወቱት፡-ከፍርድ ቤት በነጻ ተለቀው በዘመድ አዝማድ ታጅበው በፒያሳ አየተዝናኑ ሲጉዋዙ ዶሮ ማነቂያ ላይ የተያዙት፡- ጥቂት ቀደም ብሎ ታምራት ላይኔ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን አለምን ጉድ ያስኘ ድራማ በፓርላማ ውስጥ ሲጫወት ጡጦውን አንደጣለ ህጻን ,,,,*አልስማ አልመከር ብየ ስካር ስልስ.....*ወዘተ. አያለ ሲያላዝን የመስቀል ዶሮ በአንቁጣጣሽ ዶሮ አንዲሉ /አርስዎና በቦናፓርቲዝምና በመበስበስ ተረኞች ከመለስ ጋር ሆናችሁ ትስቁበት ነበር/

አቶ ስየ ኣብርሃ በሲያትል

ዶ/ር ታየ ወ/ስማያትን ከመምህራን ማህበር ፕሬዚደንትነት ለማግለል ባለመቻሉ መኖሪያ ቤታቸውን የጦር መሳሪያ ግ/ቤት ሆኖ በቴሌቪዥን ለማየት ችለናል፡-ተዘርዝሮ የማያልቅ ድራማ በማየት ሃያ አንድ ዓመት አሳልፈናል፡-ድራማው አሳዛኝ ክስተቶችንም ያካተተ ነው የበደኖን ዕልቂት አይነት ይህ ሁሉ ሲሆን አቶ ስየ አመራር ላይ ነበሩ፡-ይባስ ብለው በንግግርዎ .....አጠቅሳለሁ....(**የኢትዮጵያ ህዝብ ለሃያ ዓመታት ያገኘው ተነፃፃሪ ስላምና ይብዛም ይነስ በዚህ ወቅት ያፈራቸው ቁሳዊ አሴቶች ሊያጣ አይፈልግም**...) በማለት አቅጬን ይነግሩናል ፡-

አቶ ስየ..የትኛውን ስላም ነው የሚነግሩን.. በሃያ ዓመት የተጨፈጨፈው አና የተስደደው የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር ከአስገነጠላችኻት ኤርትራ ህዝብ ጋር ሊስተካከል አንደሚችል ያውቃሉ፡- የትኛውንስ ቁሳዊ አሴት፡-ለዘመናት ካፈራው ቤት ንብረቱና ርስቱ በመፈናቀል በገዛ አገሩ ስደተኛ የሆነባት ኢትዮጵያ ፡- ሃብት ንብረት ቀርቶ ቤተሰብ አንድ ላይ ሊኖር ያልቻለባት ኢትዮጵያ ፡- የመለስና የወያኔ ዓላማም ይኸው ነው፡- በዘር በሃይማኖት ብሎም በጎሳና በቤተስብ መከፋፈልና ፡-በታትንኖ አደህይቶ መግዛት፡-

የቴሌቭዥን ጀግናው መለስ በቲቪ ብቅ ኣያለ ካደረጋቸው ፉከራዎች አንዱ ..( <u>ያልተመቸው መንገዱን ጨርቅ ያርግለት....አዲሰአበባ ኑሮ የተወደደበት ወይም መኖር ያቃተው ወደ ገጠር ወይም ስደት ሄዶ መኖር ይችላል</u>...) በማለት በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ሲያላግጥ በመጀመሪያው አስርት አመታት አርስዎም አብረውት ነበሩ፡- አበጀህ በርታ አንጂ በሕግ አምላክ የሚለው ሰው አልተገኘም፡-

አቶ ስየ፡-የርስዎን ከሆነ የሚነግሩን ያስማማናል ሲመችዎ አሜሪካ ሲያስኙዎ ኢትዮጵያ መንሸራሸር ይችላሉና ፡- አሊያም የኢህአዴግ አባላትን ስላምና ቁሳዊ አሴት አንደሆነ አንጂ በትውልድ ቀየው መኖር አንደ ወንጀለኛ አየተደበደበ መንደሩ አየተቃጠለ የርሻ ማሳውን አየተነጠቀ በከተማ ያለውም ያያት የቅድመ አያት ቤትና ርስት አየተነጠቀ ያለው ህዝብ ግን ይህን ቃል ሊስማው አይሻም፡-ስደት በአገር ውስጥም በውጪም የዕለት ተለት ህይወት ከሆነ ሃያ አመታት ያስቆጠረ ህዝብ ፡-በውነቱ የአንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አባል ንግግር ነው ለማለት አያስደፍርም፡-

አሁንም አጠቅሳለሁ....( **አሁን በኢትዮጵያ ብቅ ያለውን ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ሽግግርን አውን ለማድረግ የተፈጠረ አጋጣሚ አድርገን ልንመለከተው አንችላለን** ...)በማለት አቶ ስየ ይነግሩናል ፡-መለስ ስለሞተ አንዴት ነው ለውጥ የሚመጣው .....የመለስ ፖሊሲ አንዲትም ነገር አትቀየርም ባለበት ይቀጥላል ኣያሉን አኮ ነው...አሽከሮቹ ፡-አርስዎም ይህንኑ አረጋግጠዋል.....ታዲያ ምን አይነት ለውጥ ይጠብቃሉ አንዴትስ በቀላሉ ወይም በምኞት ይገኛል፡-እርስ በርሱ የሚጣረስ ፅሁፍ ማቅረብዎ ኢህአዴግን ቢጠቅም እንጂ ለኢትዮጵያ ህዝብ ግን ለሌላ ሃያ አንድ ዓመት የስቃይ ዘመን አመላካች ነው

በመቀጠልም አቶ ስየ....(**በአንዳንድ ወገኖች ከታላቁ ህዝባችንና የአገራችን ወግና ስርዓት ወጣ ባለ ሁኔታ በሰው ሞት መደስት ታይቶባቸዋል.....**) ይሉናል፡- ፈጣሪ የኢትዮጵያን ህዝብ እንባ አይቶ አነሳው እንጂ መለስ ለኢትዮጵያ ህዝብ ምኑ ነው..ከጫካ አጅባችሁ አምጥታችሁ ስልጣን ላይ አስቀመጣችሁት ወላጆቹ የጣሊያን ባንዳ ሁነው ያቃታቸውን የጣሊያንን ዕቅድ በናንተ ድጋፍ አገር በታተነ ኤርትራን አስገንጥላችሁ አገሪቱን ያለ ባህር በር አስቀራችሁ የኤርትራን መገንጠል ከአለም ቀድሞ በፊርማው በማፅደቅ የመጀመሪያው ሆነ ዓለምን ጉድ አስኘ ፡-ወላጅ እናቱን ከበሮ እያስደለቀ በአገራችን ቴሌቪዥን እንድናይ በማድረግ ምን ታመጣላችሁ አለን፡- ጉድ አርጎ ፈጥሮታልና አሁንም በልማትና ግድብ ስም እንደ **ገና ዳቦ** አገር እየቆረስ በመሸጥ ላይ እንዳለ ባጭር አስቀረው እንጂ ከዚህ በኋላ የአስር ዓመት እድሜ ቢጨምርለት ኖሮ..የስይጣን ጆሮ አይስማ እንጂ የምትቀረን...ኢትዮጵ**ያ** ፊደል ብቻ ሊሆን ይችል ነበር፡-ታዲየ ባገርና በህዝብ ሲያላግጥ ለኖረ ባለጌ አምባገነን ሞት ጮቤ ያልተረገጠ ለፈጸመው ወንጀልና ግፍ፡-ዕልልታም፡- ሽለላም፡- ቀረርቶም፡- ፉከራም፡- ሌላም በተደርገ ነበር፡-ዘር በማጥፋት ወንጀል አለም አቀፍ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ መቅረቱ የሚያስቆጪ ቢሆንም ወደፊት በኔ ይሁንብዎት <u>አፅሙ ለኢትዮጵያ ህዝብ ፍርድ እንደሚቀርብ አይጠራጠሩ</u>፡-አገርና ዘርን ከማጥፋት ባሻገር የኢትዮጵያን ህዝብ ከመጠን በላይ አስቃይቶአል፡-አገራችንንና ህዝቡን አዋርዷል፡-ፈጅቶአል፡-ለስደት ዳርጎአል፡-በተለይ የአረብ ገረድ ሆነው ስብአዊ ክብራቸውን አጥተዋል፡-ውቅያንኖስ ውስጥ ስጥመዋል፡-ኮንተኔር ውስጥ ታፈነው ሞተዋል፡-ከፎቅ ላይ ተጥለዋል፡-በእሳት ተቃጥለዋል፡-የስደት ኑሮ በቃኝ ያለቺው በኢትዮጵያ ኤምባሲ በር ላይ እየተደበደበች በሃይል አስገድደው በመኪና ሲወስዱአት የመለስ አምባሳድሮች ተመልካች ሆነዋል፡-በምድር ላይ ከተፈፀሙ ዎንጀሎች ሁሉ ወደር የሌለው የዘመናችን አረመኔ ሲወገድ እንዴት አይደስት፡-

አቶ ስየ፡-የኢትዮጵያ ህዝብ ምሬት ከዚያም በላይ ነው መለስን እኮ በቴሊቪዝንና በፖስተር እንጂ በአካል የት ሲያውቀው ነው፡- ከቤተ መንግስት በወጣ ቁጥር ያዲሰአበባ ህዝብ ይደርሰበት የነበረው ስቃይ እንዴት ይረሳል፡-በየስው ግቢ እንደጥጃ ታጉሮ፡-አምቡላንስ ከመንገድ ውጣ ሲባል፡-እንደ አውሎ ነፋስ እየተምዘገዘገ የሚበረውን መለስ የት ያውቀዋል ፡-እንደ ገብረመድህን አርአያ እቅጩን መናገር ይልመዱ አለበለዚያ የመድረክ ስብስብን ጭምር ጥያቄ ውስጥ ይጥሉታል

ኣቶ ስየ ካንዴም ሁለቴ ይቅርታ እንደጠየቁ አውቃለሁ ሆኖም ይቅርታ ብቻውን በቂ ባለመሆኑና ለኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ማድረቂያ ስለማይሆን የዘገየ ቢሆንም አንድ መፅሓፍ ሊያበረክቱ ይገባል፦ ያ እስኪሆን ድረስ ግን እንደ አቶ አስገደ ገ/ስላሴ አጫጭር መጣጥፎችን በጋዜጦች ሊያደርሱን ይገባል የትግል ጓዶችዎ በህይወት እያሉ ቢሆን የተሻለ ይሆናል ማስታወሻ ውስጥ የሌለውን በመጠያየቅ የተሙአላ እንዲሆን፦ለምሳሌ መለስ ሞተ ባይጠቅመንም ስንት ጉድ በነገረን ነበር እውነቱን  አይነግረንም እንጂ፦ ስለዚህ ምንም ሳያስቀሩ ሊያሳውቁን ይገባል፦የርስዎን የፍርድ ቤት ጉዳይ በዝርዝር እንደፃፉት ማለት ነው፦

1...በረሃ በነበራችሁበት ወቅት ስለ ታስሩ፦የተገደሉ፦የትግል ኣጋሮቻችሁ

2.በስልጣን በቆዩበት አስር ዓመታት ግዜ ፦፦የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቦርድ ስብሳቢ፦የኤፈርት ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን ሲሰሩ ስለ አውሮፕላኖች ግዢ  ስለ በጀትና ሰው ሃይል አስተዳደር ..አጠቃላይ ሁኔታ፦በተለይ የአገር መከላከያ ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት የሻቢያ ጦርነት ወቅት ነው፦

3.እንዲያውም ሃየሎም አርአያ በየጊዜው በዚህ ዙሪያ እርስዎ ወደ ኤፈርት ከሄዱ በሁዋላ ከመለስ ጋር  ይጨቃጨቅ እንደነበርና የተገደለውም ከዚህ ጋር በተያያዘ  እንደነበርና ነባር ታጋዮችም ምክንያቱ ይገለፅልን የሚል ጥያቄ በማቅረባቸው ለማዘናጋት ጦርነቱ በፍጥነት ስለመጀመሩ ፦

4.ከጦርነቱ በሁዋላ አንድ ኮሎኔል የሁለት ልጆች እናት ታጋይ ሚስቱ ገድላው ራሱውዋን  አጠፋቺ ተብሎ አስገራሚ ክስተት በዜና ማስራጫወች በኢቲቪ ጭምር የተነገረው  ሃየሎም እንዴት ሞተ እያለ በተደጋጋሚ ይጠይቅ እንደነበር

5. የብአዴን ታጋይ ሙሉ ዓለም  ግድያ፦ የታምራት ላይኔ ዓለም ጉድ እስኪል ድረስ አሳፋሪ ንግግር ጉዳይ፦፦ሌሎችንም ጨምረው ንስሃ ይግቡ፦

አስጨናቂ ድረስ

Baschenaki44@gmail.com